Click Here & Upgrade
Expanded Features
Unlimited Pages
PDF Complete

# ፀረ-ኢትዮጵያ የሽብር መረብ ሲበጣጠስ

አሸባሪነትና ሽብር ፍላጎትና እምነትን በስልጡን ንግግር፣ ደርድር እና በሰላማዊ ሰጥቶ መቀበል ማስፈፀምን እምቢ ብሎ በመርገጥ ይህንኑ በዘግናኝ ህልፍትና ውድመት በብዙሀኑ ላይ የመጫን ግለሰባዊ ወይም ቡድናዊ የሆነ የጥቂቶች አባዜ ነው፡፡ አሸባሪነትና ሽብር የልዩነት፣ የመቻቻል እና ምክንያታዊነት ፀር የሆነ ደዌ ወይም በሽታ ነው፡፡ ለእናትነት፣ ለአባትነት፣ ለአያትነት፣ ለልጅነት፣ ለወጣትነት ርህራሄ የለውም፡፡ የመንግስት ተቀጣሪ ከግል ለፍቶ አዳሪ፣ ወታደርን ከሲቪል፣ የኔ ብጤን ሞልቶ ከተረፈው፣ መሪን ከምንዝር ወዘተ አይለይም፡፡ ከህፃን እስከ ሽማግሌ አይመርጥም፡፡ አሸባሪነትና ሽብር ፍጡራንና ዜጎችን በጅምላ የመቀርጠፍ ፀረ ህይወት አረመኔነት ነው፡፡

እኛ የኢትዮጵያ ህዝቦች ይህ የአሸባሪዎች የሽብር ጥቃት ዒላማ ሆነናል፡፡ የእንዲህ አይነቱ ሽብር ጥቃት ዒላማ የሆንነው ደግሞ ዋነኛ ሀገራዊ ጠላታችን ድህነት መሆኑን ለይተን፣ በስርዓትና በሀገር ደረጃ የፖሊሲዎቻችን ይዘት፣ የበጀት ምደባቸን መስፈርት እንዲሁም ተጨባጭ ትኩረታችንና እንቅስቃሴያችን ሁሉ የልማተ ስራዎችና የዴሞክራሲያዊ ተቋማት  ግንባታ ላይ ሆኖ እየተረባረብን ባለንበት ሁኔታ ነው፡፡ ከዓመት ዓመትም በኢኮኖሚው መስክ የሰፋ የህዝቦች ተጠቃሚነትን፡፡ በፖለቲካው ዘርፍ ደግሞ የጠመረ ዴሞክራሲያዊ አሳታፊነትን በማጎልበት አያረጋገጥን መጓዝን ሙጥኝ ባልንበት ወቅት ነው፡፡

በአጭሩ በሽብርና በአሸባሪዎች የተጠቃነው በመረጥነው ሀገራዊ ተግባር የተነሳ ሰላምና ሰላማዊነትን የሀገራዊ ፖለቲካችን እና የውጭ ግንኙነታችን መመሪያ ቋንቋና መዝሙር አድርገን በጥቃትም ሆነ በድል ማግስት በተጨባጭ ረጅም ርቀትን በመጓዝ ዝግጁነታችንንና ቁርጠኝነታችንን ባስመሰከርንበት ሁኔታ ውስጥ ሆነን ነው፡፡

የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት እና የፌዴራል ፖሊስ የጋራ ፀረ ሽብር ግብረ ኃይል እነዚህነ የሽብር ሙከራዎችም ሆነ የተገኙ ውጤቶች የተመለከተ ዝርዝር መግለጫ በየወቅቱ ከማቅረብ በመቆጠብ ለመቆየት የተገደደው የሽብር መረቡን አመርቂና ውጤታማ በሆነ መልኩ በጣጥሶ እንዲህ ለመቆጣጠር የመረጃና ክትትል ስራውን እና ተያያዥ የሆኑ ስልቶችን ሚስጥራዊነት አረጋግጦና ለተወሰነ ጊዜ ጠብቆ መንቀሳቀስ ግድ ስለነበረበት ነው፡፡

የጋራ ፀረ ሽብር ግብረሀይሉ አካላት ባደረጉት የረቀቀ ሙያዊ ብቃት፣ ከፍተኛ ትዕግስት እና ጥንቃቄ የተሞላበት እንቅስቃሴ አማካይነት ይኸው የፀረ ህዝብ ሽብር መረብ ከላይኛው አመራር አስኳሉ እስከ ታችኛው የሽብር አሀድ ድረስ ከሚካተቱና በስምሪትና ዝግጅት ላይ ከነበሩ ተጠርጣሪ አባላቱ ከተልዕኮና የአፈፃፀም ሰነዶችና ካርታዎቻቸው፣ ፎሮ ግራፎር፣ የኢ-ሜይል ልውውጦች እና ፈንጂዎች ጋር እጅ ከፍንጅ ተይዘዋል፡፡ ብቸኛ መነሻውና ዓላማው  ኢትዮጵታዊያንን የትርምስና የእልቂት አውድማ አድርጎ ማዳከምና ማጥፋት የሆነውን የዚህ መረብ ጥንቅር፣ በሀገር ውስጥና በውጪ ያለው መዋቅራዊ ሰንሰለት፣ የነበረው ዕቅድ፣ የተከተለውን አፈፃፀምና ስምሪት የተመለከቱ መሰረታዊ ጭብጦችና ሀቆች ለማወቅም ተችሏል፡፡ የእብሪት ወረራና ጦርነት የመቆስቆስ

Click Here & Upgrade
Expanded Features
Unlimited Pages
PDF Complete

አባዜውና አቅሙ ተመትቶ ከሚሸሽ ወዲህ፣ በአፍሪካ ቀንድ ሽብርን በዋነኛ ስልትነት፣ አሸባሪ ስብስቦችን ደግሞ በተላላኪ አጋርነት መጠቀም መለያው የሆነው የኤርትራው ሻዕቢያ የፀረ ኢትዮጵያዊው ሽብር ዋና አዝማችና አስተባባሪ መሆኑም ተረጋግጧል፡፡ ይህ በሻዕቢያ የተቀናበረና የተመራ የሽብር ጥረት እንደሚከተለው በሁለት ክፍሎች ተከፍሎ ቀርቧል፡፡

<u>አንደኛው የሽብር ስምሪት ዕቅድ</u>

§ በግንቦት 1998 ዓ.ም በሆላንድ ዩትሬክት ከተማ "ትብብር ለነፃነትና ዴሞክራሲ (ኤ.ኤፍ.ዲ)" በሚል ስያሜ በተፈጠረው ግንባር የተካተቱት የኦሮሞ ነፃነት ግንባር /ኦነግ/፣ የኦጋዴን ብሔራዊ ነፃነት ግንባር /ኦብነግ/፣ የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር /ኢህአግ/ የተባሉ ሀገር በቀልና ኤርትራ ተከል እንዲሁም ራሱን የቅንጅት ሰላም አቀፍ አመራር ብሎ በመሰየም የሚጠራና በቁጥጥር ስር ከሚገኙ ጥቂት የቀድሞ አክራሪ መሪዎች ውክልና አለኝ የሚለው የስደት ቅንጅት አሸባሪ ቡድኖች በተለያየ ደረጃ በዚህ የሻእቢያ ፀረ ኢትዮጵያ የሽብር መረበ በተላላኪነት ተሳትፈዋል፡፡

§ በሻዕቢያ ከፍተኛ ባለስልጣናት አማካይነት የእነዚህ የፀረ ኢትዮጵያ ሽብር ተላላኪ ድርጅቶቹ መሪ የሆኑ ግለሰቦች ከጥር እስከ የካቲት 1998 ባለው ጊዜ ውስጥ በአሜሪካ፣ በስዊድንና በኖርዌይ፣ ከመጋቢት 3 እስከ 4 1998 በፍራንክፈርት ጀርመን፣ ከሚያዝያ 7 እስከ 8 1998 በዱባይ መገናኘታቸው ተረጋግጧል፡፡

§ በዋናነት ይህ አንደኛው የሽብር ስምሪት እቅድ በሻእቢያ መሪነትና በኦነግ ተላላኪነት የተፈፀሙ፣ የከሸፉ እና የታቀዱ ጥቃቶችን ያካተተ ነው፡፡

§ የሽብሩ ዋነኛ ኢላማም ህዝብ በብዛት የሚያዘወትራቸው የግልና የመንግስት ተቋማት፣ በየእለቱ በስፋት የሚጠቀምባቸው የግልና የመንግስት ማመላለሻ አገልግሎቶች ናቸው፡፡

§ እጅግ አስፈላጊ ተበሎ በሽብር መረቡ በዋነኛ ተግባርነት የተካተተው ስነ ልቦናዊ ሽብር የሚያካሂደው ኦነግ፣ የቅንጅት ዓለም አቀፍ አመራርና የአርበኞች ግንባር የፀረ ኢትዮጵያ ፕሮፓጋንዳና ፖለቲካ ስራ መዋቅር መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ የፈጠራ ፕሮፓጋንዳዎችን በማሰራጨት ኢትዮጵያዊያን በስነ-ልቦናዊ ሽብርና ተስፋ መቁረጥ እንዲዘናጉ፣ ከቀቢፀ ተስፋ የሚመነጩ ብጥብጦች እንዲፈጠሩ፣ የተለያዩ መንግስታትና አካላት ፀረ ኢትዮጵያ አቋምና እርምጃ እንዲወስዱ እንዲሁም የሽብር መረብ አሸባሪ ተግባራት በትግል ስም ተሸፍኖ ከተጠያቂነት እንዲያመልጥ የማድረግ ተልዕኮ ተቀብሎ ተሰማርቷል፡፡ ከአስመራ በሚሰራጩ ሬዲዮ ስርጭቶች እና በተለያዩ ዌብ ሳይቶች የተካሄደው ፀረ ኢትዮጵያ ፕሮፓጋንዳና ዘመቻ የታቀደና የተቀናጀ የዚህ ስነ ልቦናዊ ሽብር አካል መሆኑን በግብረ ኃይሉ እጅ ከገቡ ሰነዶችና የኢ-ሜይል ልውውጦች ተረጋግጧል፡፡

Click Here & Upgrade
Expanded Features
Unlimited Pages
PDF Complete

- አስመራ፣ ጅቡቲ፣ ዱባይና ኬንያ በተቀመጡ የሻእቢያ ኃላፊዎች አማካይነትም ለኢህ የሽብር እቅድ ተፈፃሚነት ተፈላጊው አመራር፣ ገንዘብ፣ ፈንጂዎች እና ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

- አስመራ የሚገኘው የኦሮሞ ነፃነት ግንባር /ኦነግ/ አመራርም ጥቃቱን ለመፈፀም አስፈላጊውን የሀገር ውስጥ መዋቅር በመዘርጋት፣ ፈንጂዎችን ጨመሮ የተፈላጊ ግብዓቶችን ወ.ዘ.ተ... በማቅረብ የቅድመ ስምሪት ስራ በተላላኪነት አስተባብሯል፡፡

- አነዚህን ተግባሮች ያከናወነው የኦነግ የሽብር መዋቅር 12 አባላት ያሉት ሲሆን፣ የሽብር ቡድኑ ካከናወናቸው ተግባሮች መካከል የመዋቅር ዝርጋታና የመረጃ ማሰባሰብ፣ የፈንጂ አቅርቦትና ለፍንዳታ ዝግጁ አድርጎ በመጥመድ ማፈንዳት፣እንዲሁም የጥቃት ስምሪት እና የድህረ ጥቃት ማፈግፈጊያ ቦታዎችን፣ ትራንስፖርት ወ.ዘ.ተ... ማመቻቸት የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

- በዚህ የኦነግ አሸባሪዎች መዋቅር አማካይነትም በዚሁ ወቅት ተጠምደው በአዲስ አበባ የተለያዩ ክፍለ ከተማዎች የፈነዱ ፈንጂዎች በአጠቃላይ ብዛት 34 /ሰላሳ አራት/ነው፡፡

- ይህንንም የተወጡት የኃላፊነት ክፍፍል ያደረጉ የሚከተሉት የቡድኑ አባል የሆኑ ተጠርጣሪ አሸባሪ ግለሰቦች ናቸው፡፡

- ታደሰ ፉፋ፣ በዚሁ ወቅት በአሸባሪው ቡድን ከጥቅም ላይ የዋሉ ብዛታቸው 13 የሆኑ ፈንጂዎችን ደብቆ በመያዝ ወደ አዲስ አበባ ያስገባ እና በቁጥጥር ስር የሚገኝ፣

- ዱላ ሞቲ፣ ከህዳር 1998 እስከ መስከረም 1999 ባለው ጊዜ በአሸባሪ ቡድኑ ከተፈፀሙ ፍንዳታዎች መካከል በአውቶቡስ መናኸሪያ፣ ሰባተኛ በሚገኝ ኬክ ቤት፣ በላሊበላ ሬስቶራንት፣ በባቡር ጣቢያ፣ በሪቼ አካባቢ ግንብ ስር እና ካራ ቆሬ አካባቢ ባለመንገድ ዳር የፈነዱ ስድስት የፈንጂ ጥቃቶችን የፈፀመ፣ በቁጥጥር ስር የሚገኝ፣

- አበበ ግርማ፣ ከቡድኑ ጋር በመረጃና ድጋፍ ዘርፍ የሚንቀሳቀስ እና አብዮት አለማየሁ የተባለውን ተጠርጣሪ አሸባሪ መስከረም 4 ምሽት ከተመፀመ የፍንዳታ ሙከራ በኋላ ወደ ቤቱ ወስዶ በመደበቅ ያስመለጠ፣ በተጨማሪም በተለያዩ ፍንዳታዎች ፈፃሚነት የሚጠረጠር እና በቁጥጥር ስር የሚገኝ፣

- አረቦ መገርሳ፣ በቡድኑ የሽብር እንቅስቃሴ የተጠመዱና ለፍንዳታ ዝግጁ የሆኑ ፈንጂዎችን በማጓጓዝ የተሳተፈ፣ በቁጥጥር ስር የሚገኝ፣

- ጴጥሮስ ታደሰ፣ ጎሳዮ ቦንሳ እና ደሳለኝ መገርሳ፣ የከለላ ቦታዎችን የሚያመቻቹ፣ ተመሳሳይ የትራንስፖርት ድጋፍ የሚሰጡ ነበሩ፡፡ በተለይ ደሳለኝ መገርሳ የተባለው ተጠርጣሪ ከመስከረም 4 ፍንዳታ በኋላ አብዮት አለማየሁ

Click Here & Upgrade
Expanded Features
Unlimited Pages
PDF Complete

የተባለውን አሽባሪ ጎሳዮ ቦንሳ ከሚባለው ሌላ ተጠርጣሪ ቤት በሌሊት አውጥቶ ወደ ሻሸመኔና ሀገረ ሰላም ያሸሸ፡፡ ሦስቱም በቁጥጥር ስር ውሏል፡፡

§ አብዱራህማን ወዮ፣ /ለሽብር መረቡ የስምሪት ማዕከል በመሆን ያገለገለውን ቦታ በሱቅ ሽፋን ካራ ቆሬ በሚባለው አካባቢ አቋቁሞ የመራ፣ የፈንጂዎቹን የሰዓት ማቀጣጠያ አቀናብሮ በማዘጋጀት ለፈፃሚ አሸባሪዎች የሚሰጥ ብቸኛ ችሎታ የነበረው፣ ከዚህ ባለፈው በፒያሳ መብራት ኃይልና አየር መንገድ ቢሮዎች ላይ የተፈፀሙትን ሁለት የፈንጂ ጥቃቶች ያከናወነ፡፡ በመጨረሻም ይህንኑ ተግባሩን በካራ ቆሬ ሱቁ ውስጥ ሲያከናውን መፈናፈኛቸውን ከቀን ወደ ቀን እያጠበበባቸው በመጣው የፀረ ሽብር ግብረ ኀይሉ ክትትል የተጨነቀ ጥድፊያ ውስጥ በመግባቱ እና ሻእቢያ ሆን ብሎ የፈንጂ ሰዓት መቆጣጠሪያውን ሞዲፊክ በማድረጉ ምክንያት ፈንጂው የሚፈነዳበትን ጊዜ መገመት ወይም ማወቅ ባለመቻሉ የተነሳ ፈንጂው ፈንድቶበት መስከረም 4/1999 ህይወቱ ያለፈ

§ <u>ወንደሰን ወንድሙና ከፈኔ ገቢሳ፡-</u> በበርካታ ቦታዎች ላይ ከደረሰ የሽብር ጥቃት በተያያዘ የሚጠረጠሩ፣ በእርግጠኝነት በሦስት ቁጥር ማዞሪያ አካባቢ በ77 ቁጥር አንበሳ የከተማ አውቶቡስ፣ በአንድ ታክሲ፣ እና አብነት አካባቢ በሚገኝ ዘበኛ ቤት የደረሰውን የፈንጂ ጥቃት የፈፀሙ ተጠርጣሪዎች ናቸው፡፡ በመሰል የሽብር ስምሪት ላይ እያሉ በጋራ ፀረ ሽብር ግብረ ኃይሉ ክትትል መፈናፈኛ ከቀን ወደ ቀን እያጠበበባቸው በመጣው የፀረ ሽብር ግብረ ኃይሉ ክትትል የተጨነቀ ጥድፊያ ውስጥ በመግባቱ እና ሻእቢያ ሆን ብሎ የፈንጂ ሰዓት መቆጣጠሪያውን ሞዲፊክ በማድረጉ ምክንያት ፈንጂው የሚፈነዳበትን ጊዜ መገመት ወይም ማወቅ ባለመቻላቸው የተነሳ ፈንጂው ፈንድቶባቸው መስከረም 4/1999 ህይወታቸው ያለፈ፣

§ <u>ከፍያለው ተፈራ፡-</u> በንፋስ ስልክ ላፍቶ በሎንቺና መኪና ውስጥ የደረሰውን ፍንዳታ የፈፀመ፣ በተመሳሳይም በጋራ ፀረ ሽብር ግብረ ሀይሉ ክትትል መፈናፈኛ በማጣት በመስከረም 1999 የተሰጠውን መሰል ጥቃት ቦታ ቀይሮ በመፈፀም አደጋ አድርሶ ለመሸሽ በጥድፊያ ላይ ሆኖ ከቀን ወደ ቀን እያጠበበባቸው በመጣው የፀረ ሽብር ግብረ ኃይሉ ክትትል የተጨነቀ ጥድፊያ ውስጥ በመግባቱ እና ሻእቢያ ሆን ብሎ የፈንጂ ሰዓት መቆጣጠሪያውን ሞዲፊክ በማድረጉ ምክንያት ፈንጂው የሚፈነዳበትን ጊዜ መገመት ወይም ማወቅ ባለመቻሉ የተነሳ ፈንጂው ፈንድቶበት ሁለት እግሮቹን ያጣ፣ በቁጥጥር ስር የሚገኝ፣

§ ለሽብር ሰልጥነው ጥቃት የሚያካሂዱ፣ ለተልዕኮው መፈፀም የመኖሪያና መደበቂያ ቦታ የሚያመቻቹ፣ የፈንጂ፣ የቦምብና የመሳሪያ ግዥ አከናውነውና ተቀብለው የሚያከማቹ እንዲሁም መረጃዎች የሚያሰባስቡ 14 /አስራ አራት/ ተጠርጣሪ ግለሰቦች በዚሁ ዙር በማሰማራት ኦነግ ተልዕኮ ተቀብሎ ተንቀሳቅሷል፡፡

§ አብዲሳ ሄርጌሳ፣ ሽመልስ ተስፋዬ፣ አበራ ነዳ፣ በዳዳ ደንደና፣ ዘሪሁን ካሳሁን፣ ናትአን አብዶ፣ ደረጀ ፉፋ፣ ሰለሞን በቀለ፣ ኩምሳ ገሬ፣ አወል አባቡልጉ፣

Click Here & Upgrade
Expanded Features
Unlimited Pages
PDF Complete

ታረቀኝ ዋጋሪ፣ አዱኛ ደበሌ፣ ንጉሤ ጋሮምሳ፣ ግዛው ገቢሳ፣ አላማየሁ ሰርቤሳ እና አዱኛ መገርሳ የተባሉት የዚሁ የኦነግ መዋቅር ተጠርጣሪ አባላት ናቸው፡፡

§ አብዮት አለማየሁ፡- የሽብር ቡድኑን ከአብዱደራህማን ወዮጋር በመሆን መርቷል ተብሎ የሚገመት የሽብር ጥቃቱን ከሚመራው የኦነግ ከፍተኛ አመራር ጋር ግንኙነት በማድረግ ፈንጂዎችን ያመላለሰ፣ በአውቶቡስ ተራ አካባቢ በሚገኘው ሚጣቅ ሆተል እና በካራ ቆሬ መብራት ኃይል መስሪያ ቤት ፊት ለፊት የደረሱትን ፍንዳታዎች የፈፀመ፡፡ ያልተያዘ

<u>ከዚህ የአሸባሪዎች ጥቃት በመነጨም፡-</u>

- ስድስት ሰላማዊ ዜጎች ህይወታቸው አልፏል፡፡
- እስከ መቶ የሚደርሱ ወገኖቻችን ከከባድ እስከ ቀላል አካላዊ ጉዳት ደርሶባቸዋል፡፡
- ከደሀው ህዝብ በተሰበሰበ ቀረጥ የተገነቡ ልዩ ልዩ ተቋማትና ንብረቶች ተጎድቷል፣ ወድመዋል፣
- ዜጎች ቀን ከሌሊት ሰርተው እና ገንዘባቸውን ቆጥበው ያፈሯቸው አገልግሎት ሰጪ ታክሲዎች፣ ሱንቺናዎች፣ የጭነት ካሚዎኖች እና የንግድ ተቋማት ላይ ጉዳት ደርሷል፡፡ የተወሰኑትም ሙሉ በሙሉ ከጥቅም ውጪ ሆነዋል፡፡ ቁሳዊ ጉዳቱ ብቻ በገንዘብ ሲተመን ከአስር ሚሊዮኖች ያለፈ ዋጋ አለው፡፡

የመጀመሪያው ስምሪት የሻእቢያ ተላላኪ የሆነው ይህ የኦነግ አሸባሪ ቡድን፣ በጋራ ፀረ ሽብር ግብረ ኃይሉ ክትትል መፈናፈኛ አጥተው በመደናገጥ ሻእቢያ ሆነ ብሎ የፈንጂ ሰዓት መቆጣጠሪያውን ሞዲፊክ በማድረጉ ምክንያት ፈንጂው የሚፈነዳበትን ጊዜ መገመት ወይም ማወቅ ባለመቻላቸው የተነሳ ሶስት አባላቱ ፈንጂው እላያቸው ላይ ፈንድቶ ህይወታቸው በስምሪት ላይ በማለፉ፣ አንድ ተጠርጣሪ አባሉም በተመሳሳይ ሁኔታ በተፈጠረ አደጋ ተጎድቶ እሱን ጨምሮ ስምንት ተጠርጣሪዎች በቁጥጥር ስር ሊውሉ በቅተው ሙሉ በሙሉ እቅዳቸው እንዲከሽፍ ሆኗል፡፡ ከዚህ ውስጥ ያመለጠ አንድ ብቻ ነው፡፡

በሻእቢያ መሪነትና በኦነግ የሀገር ውስጥ ተላላኪነት በተካሄደ የሽብር ስምሪት እስከ መስከረም 1999 ባሉ ወራቶች በአዲስ አበባና በተወሰኑ ጥቂት የሀገሪቱ ከተሞች ተፈፃሚ እንዲሆን የተቀመጠው የፍንዳታ እቅድና ግብ እጅግ አደገኛ ነበር፡፡ ይሁንና መረጃዎች እንደሚያሳዩት ከፍንዳታ ጉዳት እና ከፍንዳታ መጠን አንፃር የሽብር ቡድኑ የተቀመጠለትን ግብ መተግበርና ማሳካት አልቻለም፡፡ ከዚህ አኳያ የሽብር ቡድኑ በዚህ የስምሪት ወቅት የሞከረው የጥቃት ብዛት፣ ለዚህ ታቅዶ በመንገድ ላይ እያለ በቁጥጥር ስር ሊውል

Click Here & Upgrade
Expanded Features
Unlimited Pages
PDF Complete Documents

የበቃው ፈንጂና አቀጣጣይ ብዛት፣ የፈንጂዎቹ አይነትና መጠን ዋነኛ አስረጂ ናቸው፡፡ ይህም የሚከተለውን ይመስላል፡፡

ሀ/ በአሸባሪዎቹ ተጠምደው የፈነዱ ፈንጂዎች፡-

1. በአዲስ አበባ የተለያዩ ክፍለ ከተማዎች የፈነዱ፣ አጠቃላይ ብዛት 34 /ሰላሳ አራት/ ሞጆ፡- አጠቃላይ ብዛት 3 /ሦስት/፣ ቆቃ በሚገኝ የአበባ ልማት ድርጅት ላይ ብዛት 2/ሁለት/ በሐረር ከተማ፡- አጠቀላይ ብዛት 6/ስድስት/

በጠቅላላው 45 /አርባአምስት/ የሆኑ ፍንዳታዎች ተፈጽመዋል፡፡

ለ/ በመጓጓዝ ላይ እያሉ እና በተከማቹበት ቁጥጥር ስር የዋሉ ፈንጂዎች፡-

1. በግንቦት 97 ሀገራዊ ምርጫ ሂደት ማለትም ከሚያዝያ 1997 እስከ ሐምሌ 1997 የተያዙ ፈንጂዎች ብዛት 43/አርባ ሶስት/

   አቀጣጣይ ታይመሮች፣ ከምሱሮች ወ.ዘ.ተ.... ብዛት 47

2. ከመስከረም 1998 እስከ መስከረም 1999 የተያዙ ፈንጂዎች ብዛት 23/ሃያ ሦስት/

   አቀጣጣይ ታይመሮች፣ ከምሱሮች ወ.ዘ.ተ... ብዛት 69/ስልሳ ዘጠኝ/

በአጠቃላይ ብዛታቸው 66- ሲ-4 ፈንጂዎች እና በተመሳሳየ 116 የተለያየ ይዘት ያላቸው ማፈንጃ አቀጣጣዮች በቁጥጥር ስር ውሏል፡፡

## ሁለተኛው የሽብር ስምሪት ዕቅድ፡-

የመጀመሪያው ዙር ፀረ ኢትዮጵያ ሽብሩ በፈለገው መጠንና ዓይነት- ያልተሳካለት ሻእቢያ፣ ሁለተኛው ዙር የሽብር ስምሪት ለበለጠና ለተፋጠነ ጥፋት እንዲበቃ የተሻሻለ ይዘት እና የታቀደ አካሄድ ያው ሆኖ እንዲከናወን ሞክሯል፡፡ በተሳታፊ አሸባሪዎች ትብብርና ጥንቅር፣ በፈንጂ፣ በመሳሪያዎችና በፈንጂ ማቀጣጠያዎች፣ ሙከራውን በፖለቲካዊ ዘመቻና ፕሮፓጋንዳ በማጀብ ወ.ዘ.ተ ከፍተኛ የአይነት መጠን ለውጥ ታይቷል፡፡

ይህን በተመለከተ መንግስት በነበረው መረጃ በቁጥጥር ስር ከዋሉ ተጠርጣሪዎች ቃል እና ሌሎች ማስረጃዎች የሚከተሉት ሀቆች ተረጋግጠዋል፡፡

- ሁለተኛው የሽብር ስምሪት እቅድ ከሚያዝያ 1998 አንስቶ ከሸፈበት ጥር 1999 ድረስ ባለው ጊዜ የታቀዱ የሽብር ጥቃቶችና እንቅስቃሴዎች ይሸፍናል፡፡

- በዚህ መሰረት ባሳለፍነው ጥር በደማቅ ሁኔታ አዲስ አበባ ላይ ተካሄዶ የተጠናቀቀው የአፍሪካ መሪዎች ጉባኤ በዚህ የሻእቢያ ሁለተኛው የሽብር

Click Here & Upgrade
Expanded Features
Unlimited Pages
PDF Complete

ስምሪት እቅድ አንድ ዒላማ የነበረ ሲሆን፣ ይህም ስብሰባው በሚካሄድበት ወቅት በመዲናችን ሁከትና ስጋት ለመፍጠር፣ በሆቴሎች፣ በዋና ዋና መንገዶች፣ በመንግስት ባለስልጣናትና ተቋማት ላይ ያነጣጠረ የፈንጂ አደጋ ለማድረስ የታለመ ነበር፡፡

Ø የፀረ ኢትዮጵያው ሽብር መረብ በሻእቢያ ከፍተኛ አባላት ቀጥተኛ ቁጥጥር ስር ሆኖ በተጠናከረ መልክ እንዲከናወን ተወሰነ፡፡ ለዚህም ቀደም ካሉት ዓመታት አንስቶ በመሰል ፀረ ኢትዮጵያ ተግባራት አስተባባሪ የነበሩት ኮ/ል ፍጹም ይስሀቅ፣ ኮ/ል ጣዕመና ኮ/ል ስለሞን የተባሉ የሻእቢያ ከፍተኛ የመከላከያ ደህንነት ባለስልጣናት ለፀረ ኢትዮጵያው ሽብር መረብ በኃላፊነት እንደተመደቡ የተሰበሰበ መረጃ፣ የተገኙ ዶክመንቶችና የተያዙ ተጠርጣሪዎች ቃል ያሳያል፡፡

Ø ይህን አዲስ እቅድ ለመተግበር እንዲያስችላቸው አንድ የኤርትራ የፈንጂ ባለሙያ ወደ አዲስ አበባ በሽፋን እንዲገባ ተደረገ፡፡ ይህ የፈንጂ ባለሙያ ትክክለኛ ስሙ ሳሙኤል ኅይቶም ክፍሌ የተባለ ነው፡፡ የሳዋ 7ኛ ዙር የውትድርና ስልጠና የወሰደና የሰራዊት አባል የሆነው ግለሰብ ተልዕኮውን የተቀበለው፣ ሪፖርት የሚያቀርበውና ስምሪቱን በተመለከተ ቀጥተኛ ግንኙነት የነበረው ከኮ/ል ፍፁም ይስሐቅ፣ ኮ/ል ስዩም እና ኮ/ል ጣዕመ ከተባሉ የአጠቃላዩ ፀረ ኢትዮጵያ ሻእቢያ መራሽ የሽብር ስምሪት ዋና ኃላፊዎች ጋር ነው፡፡ ወደ ኢትዮጵያ የገባውም ከአስመራ ዱባይ፣ ከዱባይ ጅቡቲ ተጉዞና በድሬዳዋ በኩል አድርጎ ሲሆን፣ ይህንን ጉዞውን በማቀናበርና ለሽብር ጥቃቱ የሚውሉ ፈንጂዎችን በመያዝ ከጅቡቲ አብሮት ከተጓዘ ኢትዮጵያዊ ተጠርጣሪ ሽብርተኛ ጋር ነው፡፡

Ø ተጠርጣሪው ኤርሚያስ ታደሰ፡- መንግስቱ ይልማ እንዲሁም ማሙሽ አዳሙ በሚል ሶስት የሀሰት ማንነትና ስያሜ የተለያዩ ቀበሌዎች መታወቂያ ያወጣ እንደነበር ተረጋግጧል፡፡ ከዚህ የሀሰት ስያሜ አንዱን በመጠቀምም ኤርሚያስ ታደሰ በሚል የኢትዮጵያ ፓስፖርት አውጥቷል፡፡ እነዚህን ኢትዮጵያዊ የሀሰት ማንነትና መጠሪያ ተጠቅሞ በነቀምት፣ በአሶሳ እንዲሁም ናዝሬት ከተሞች ተዘዋርሯል፡፡

Ø ይህ የሻእቢያ መዋቅር፣ ሳሙኤል ኅይቶም ክፍሌን ጨምሮ ተልዕኮ ተፈፃሚነት ኢትዮጵያዊያን ቅጥረኞችን ያካትታል፡፡

Ø በገንዘብና ጥቅም ተገዝተው ዜግነታዊ ክብራቸውን ከማዋረድ ባሻገር የራሳቸውን ቤተሰቦች፣ ዘመዶችና ወገኖች የሽብር ጭዳ ለማድረግ የተባበሩ ተጠርጣሪ ኢትዮጵያዊያን ጌታሁን ዮሐንስ/ታምሩ በሚል የሚታወቅ/፣ ታፈሰ ደምሴ ደስታ፣ አበበ መንግስቴ፣ እንድሪስ፣ ይልማ ገብሬ፣ እንዲሁም ጌታቸው ኃይሌ የተባሉ ናቸው፡፡

Ø በግዥ ለሽብር የተመለመሉት እነዚህ ተጠርጣሪዎች በሙሉ ከሳሙኤል ኅይቶም ክፍሌ እና ከመስፍን አበበ እጅ የሀገር ውስጥና የውጭ ስልኮች፣ የተለያየ መጠን ያለው የዶላርና የብር ክፍያ ተቀብለዋል፡፡ ከዚሁ የሽብር ተልዕኮ በተያያዘም

Click Here & Upgrade
Expanded Features
Unlimited Pages
PDF Complete

የተወሰኑት ወደ ጅቡቲና ዱባይ ተጉዘዋል፡፡ በቆይታቸውም የሽብሩ መሪ ከሆኑ የሻእቢያ ኃላፊዎች ጋር ተገናኝተዋል፡፡ የሽብር ተግባሩን ከፈፀሙ በኋላም ወደ ፈለጉበት ውጭ ሀገር እንደሚወጡ ቃል ተገብቶላቸው እንደነበር ተረጋግጧል፡፡

Ø ይህ የሻእቢያ አባላትና የቅጥረኛ ተጠርጣሪዎች የሽብር መዋቅር ለጥቃት ካዘጋጃቸው ፈንጂዎችና የተለያዩ ቁሳቁሶች ጋር በቁጥጥር ስር ውሏል፡፡ በተመሳሳይ በዚሁ ዙር ተሳታፊ የነበረው የኦነግ ተላላኪ አሸባሪዎች መዋቅርም ከሁለት አባላቱ በስተቀር ሁሉም ተጠርጣሪዎች የተከታተሉትን ወታደራዊ ስልጠና ከሚያሳዩ ሰነዶች፣ ከተፃፃፏቸው የኢ-ሜይል መልእክቶች፣ ለመሰል ስምሪት ከተደራጁ አባላት ዝርዝር፣ ከስድስት ቦምቦች እና 400 ጥይቶች ጋር በቁጥጥር ስር ውሏል፡፡

Ø ሻእቢያ በመዲናችን ከሚያደርገው የሽብር ጥቃት ሙከራ ባሻገር ራሱ ባቋቋመው የአርበኞች ግንባር በሚል የሚጠራው የፀረ ሰላምና የአሸባሪ ቡድን አባላትን በሱዳን በኩል በማስረግ በሁመራ ከተማ እና አካባቢ ህዳር 5 ቀን 1999 ዓ.ም አይጋና ሰምሀል በተባሉ የሁመራ ሆቴሎች ላይ፣ ህዳር 14 ቀን 1999 ዓ.ም ወደ ሱዳን በሚመላለሱ ኮድ 3-22750 በሆነ መኪና ላይ፣ ህዳር 9 ቀን 1999 ዓ.ም ከሌሊቱ 8፡00 ሰዓት ቆሞ በነበረ አይሱዙ መኪና ላይ የተሞከረ የፈንጂ ጥቃቶች ለማድረስ ተንቀሳቅሷል፡፡

Ø ኦጋዴን ብሔራዊ ነፃነት ግንባር ብሎ ራሱን የሚጠራው ስብስብም የሶማሊም እስላማዊ ፍርድ ቤቶች አክራሪ የሽብር ክንፍ እና የሻእቢያ የጨመረ ግንኙነት ተከትሎ በምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ፈንጂዎችን የማመላለስ፣ ጥቃቶችንም የማድረስ ተልዕኮ ተቀብሎ ተንቀሳቅሷል፡፡

Ø ይህ ሁሉ የሻእቢያ ፀረ  ኢትዮጵያ ዱለታና ሴራ ሙሉ በሙሉ ከሽፎ በመዲናችን የተፈለገው የአፍሪቃ መሪዎች ጉባኤ በሰላምና በድል ተጠናቅቋል፡፡ ዜጎች በአጠቃላይ ከጋራ ፀረ ሽብር ግብረ ኃይል ጋር በስፋት ተባብረው ባደረጉት እንቅስቃሴም ለጥቃቱ ተዘጋጅተው የነበሩ 28 ሲ-4 ፈንጂዎች፣ 60 ፈንጂ ማቀጣጠያ ካምሱሮች በዚህ ወቅት ከጥቅም ላይ ሳይውሉ ከተያዙ የሽብር ግብዓቶች መካከል ዋናዎች ናቸው፡፡

Ø ሻእቢያ እነዚህ ሀገር በቀል ተላላኪዎቹ ተግባራቸውን ለመፈፀም ከለላ አድርገው ለመጠቀም በዋናነት የተመቻቸው ህገ መንግስታዊ ዋስትና አግኝተው በሀገራችን የተረጋገጡና የህግ ጥበቃ የሚደረግላቸውን መብቶችና አካሄዶች ነው፡፡ ከእነዚህ መካከል የዜጎች በነፃነት የመንቀሳቀስ፣ ሀሳብን የመግለፅና ተሰባስቦ የመምከር ፖለቲካዊ መብቶች አንደኛው ነው፡፡

Ø የጋራ ፀረ ሽብር ግብረ ኃይሉም ሆነ ሌሎች የፀጥታ አስከባሪ ኃይሎች ይህን በውል ተገንዝበውና አክብረው በመንቀሳቀስ ሻእቢያና ተባባሪዎቹ ለጭጉብን ያሰቡትን ህግና መብትን የመሸራረፍ አደጋ አስቀርተዋል፡ ይልቁንም የእነዚህ መብቶች ባለቤትና ተጠቃሚ የሆኑት ብዙሀን ኢትዮጵያዊያን ባደረጉት ንቁ ተሳትፎ የሽብር መረቡ በሁሉም ደረጃ እንዲጋለጥና እንዲበጣጠስ ለማድረግ

Click Here & Upgrade
Expanded Features
Unlimited Pages
PDF Complete

ተችሏል። ለዚህም አኩሪ ተግባር ያለንን ከፍተኛ አክብሮትና አድናቆት መግለፅ እንሻለን።

Ø እንዲህ በተራ ጥቅም ተደልለው የራስን፣ የቤተሰብን፣ የህብረተሰብን እና የሀገርን ደህንነትና ሰላማዊ ህይወት ለፍሬ የለሽ ጥፋት ለሚዳርግ ሽብር አሳልፈው የሚሰጡ ገለሰቦች የማህበረሰብ እና የትውልድ አሜኬላ ናቸውና በማህበረሰቡም ሆነ በህግ ፊት መቼም ቢሆን ተገቢና ተመጣጣኝ ቅጣት ሊያገኙ ይገባል።

Ø ከዚህ ቀጥተኛ ተሳታፊነት በመለስም በአንዳንድ ዜጎች ዘንድ የሚንፀባረቁ ተከታዮቹ ጎጂ ባህሪያትም ሊታወቁና በአፋጣኝ ሊታረሙ ይገባል።

Ø ከምን አገባኝ ስሜት በመነጨ ተባባሪና ተሳታፊ የሆኑ ገለሰቦችን እያወቁ ማለፍ፣

Ø ተጠቅልለው የሚጣሉ ጥቅሎችን፣ ያልተለመዱ ፀጉረ ልውጦችን እና እንቅስቃሴዎችን በቸልታ ማለፍ፣

Ø ማንነትን ሳያጣሩና ሳያረጋግጡ ጥቅምና ገቢን በማየት አሸባሪዎች በመጠለያነትና መሸሸጊያነት የሚጠቀሙበትን ቤት ወይም ማረፊያ ማከራየት፣

Ø በተመሳሳይ ይህንኑ ማንነት ሳያረጋግጡና ከሚመለከታቸው አካላት ተፈላጊ መረጃ ሳይጠይቁ መኪና ማከራየት፣

Ø የሞባይል ስልኮችን ማንነትን ሳያረጋግጡ ለሌላ በኪራይም ሆነ በተውሶ ማስተላለፍ እና ተጥለው ወይም ተረስተው አገኘሁ በሚል ለፖሊስ ሳያሳውቁ ማንሳት፣ እንዲሁም

Ø የቀበሌ መታወቂያ ካርድን በገንዘብም ሆነ በሀሰት ምስክርነት መስጠትና እንዲሰጡ መተባበር የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

ሁሉም ዜጋ በባለቤትነትና ወገናዊ ስሜት በመንቀሳቀስ ተገቢ መረጃዎችን በወቅቱ በአቅራቢያው ለሚገኙ የፀጥታ አስከባሪ ኃይሎች ማሳወቅ፣ አልፎም በሁሉም መልኩ መተባበር ይጠበቅበታል፣ ከዜግነታዊ መብቱ የሚመነጭ ግዴታው ነውና። ይህን ዓይነት ተፈላጊ የሆነ ወቅታዊ የግልና የጋራ ባህሪ እርምትን መሰረታዊ ከሆነው የልማት ጥረታችን ጋር አቀናጅተን ከተጓዘን ሽብርን ከምንጩ የማድረቅ ሰፊ አቅም እንደሚኖረን እርግጠኞች ነን፣

በመጨረሻም የእነዚህን ተጠርጣሪ ሽብርተኞች የምርመራ ውጤትና ሂደት በየወቅቱ እንደምናቀርብ እየገለፅን፣ የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት እና የፌዴራል ፖሊስ የጋራ የፀረ ሽብር ግብረ ኃይል እንደ ትላንቱና እንደ ዛሬው ሁሉ ወደፊትም ሻእቢያን ጨምሮ የማንኛውንም ወገን ፀረ ኢትዮጵያ የሽብር መረብ በታማኝነት፣ በሙያዊ ብቃትና ውጤታማነት ለመበጣጠስ እንደሚሰራ ያረጋግጣል።

በብሔራዊ የመረጃና ደህንነት አገልግሎት እና

Click Here & Upgrade
Expanded Features
Unlimited Pages
PDF Complete

በፌዴራል ፖሊስ ፀረ-ሽብር ግብረ ኃይል

ተዘጋጅቶ የቀረበ

የካቲት/ 1999 ዓ.ም